# የአፍሪቃን የጠለቀ ችግር ለመወያየት

*በአ.አ ከ29-10 እስከ 31.10.2009*

## ስብሰባ ተካሄደ! እኛስ ምን እየሰራን ነው?

*መግቢያ*

የአፍሪቃን የጠለቀ የኢኮኖሚ ፣ የማህበረሰብ ፣ የአካባቢ ቀውስ ፣ የሴቶች ጥያቄና ፣ በተለይም በወጣት ሴቶች ላይ ስለሚደርሰው በደል ፣ ሰለመንግስት አስተዳደርና ስለሙስና ፣ ሊትሬቸር አንድን ጨቋኝ አገዛዝ ለመዋጋት ስለሚኖረው ሚናና አንድን ህዝብ ንቃተ-ህሊናውን ከፍ ለማድረግ ስለሚጫወተው ተግባር ፣ የአንድ አገር ቋንቋ በሰው አስተሳሰብ ጥልቀትና እንዲሁም በጠቅላላው የህብረተሰብ ዕድገት ላይ ስለሚኖረው ሚና ፣ስለዕድገት ምንነትና ያሉትን የተወሳሰቡ ችግሮች በማቲማቲካል ሞዴሎችና በሌሎችም የተወሳሰቡ (Multivariant Solution) ዘዴዎች መፍታት ስለሚቻልበት ሁኔታ ለመወያት ፣... ወዘተ. በበርሊን ከተማ በታወቀው በሁምቦልድ ዩኑቨርሲቲ ውስጥ ስብሰባ ተካሄዷል። ይህንን ሶስት ቀን የፈጀ ግሩም ስብሰባ ያዘጋጁት በጀርመን በተለያዩ ከተማዎች የሚኖሩ የአፍሪቃ ምሁሮችና ተማሪዎች ሲሆኑ ፣ በስብሰባው ላይ ለመካፈልና ስለ የአገሮቻቸው የተወሳሰበ ችግር ትምህርታዊ መግለጫ ለመስጠት የተጋበዙ ብዙ ምሁራን ከአፍሪቃ ፣ በተለይም ከናይጀሪያ ፣ ከአሜሪካና ከተለያዩ የአውሮፓ አገሮች የሚኖሩ አፍሪቃዊ ምሁራን በመገኘት ከዚህ ቀደም ታይቶ የማይታወቅ ሰፊና የጠለቀ ትምህርታዊ ትንተና በመስጠት የቱን ያህል ለአህጉራቸው እንደሚያስቡ አረጋግጠዋል። ይህ ጸሀፊ ሶስት ቀን በተሳተፈበት ጊዜያት የተገነዘበው ፣ የተጋበዙት የአፍሪቃ ምሁራን አዳማጭና ትችትን ተቀባይ ብቻ ሳይሆኑ ፣ ከምን ጊዜውም በበለጠ በጠለቀና ሰፋ ባለ ዕውቀት እንደታጠቁና ፣ ከሳይንስና ከሌሎች የህብረተሰብ ሳይንስ አንጻር የአፍሪቃን ችግር እንዴት ለመፍታት እንደሚቻል የጠቆሙበት ታላቅ ስብሰባ ነው።

በዚህ በበርሊን ከተማ የአፍሪቃ ሁኔታ ያገባኛል በሚሉ ፣ በየጊዜው አፍሪቃ በሚመላለሱ የዕርዳታ ሰጪ ድርጅቶች ወኪሎችና ተቀማጭነታቸው እዚሁ በርሊን በሆኑ ምሁራንና ኢንስቲቱሽኖች አማካይነት ተመሳሳይ ስብሰባዎች ተካሂደዋል። ይካሂዳሉም። በእንደዚህ ዐይነቱ በጀርመን ኢንስቲቱሽኖች በሚደገፈው ስለአፍሪቃ ችግር ለመወየያት በሚደረገው ስብሰባ ላይ ስለአህጉራችን ችግር ሳይንሳዊና ጠለቅ ያለ ውይይት ሲካሄድ ታይቶ አይታወቅም። አዘጋጆቹ ከመጀመሪያውኑ ከራሳቸው በጥቅም ጋር የተሳሰሩ ፣ ወይም የተወዳጁትንና አንድ ዐይነት አመለካከት ያላቸውን ስለሚጋብዙ ፣ አብዛኛውን ጊዜ ስብሰባው አሰልቺና ተደጋጋሚ እንዲሁም ለችግሩ መፍትሄ ሰጪ ስብሰባ አይሆንም። በተጨማሪም ሳይንሳዊ ዘዴንና ፈለግን የተከተለ አይደለም። ሁለተኛም ፣ በስብሰባው ላይ ተገኝቶ ሰለ አፍሪቃ የኢኮኖሚና የማህበረሰብ ችግር ለየት ያለ ትንተና ለመስጠት የሚሻውን ቶሎ ብለው ስለሚዘጉት ሳይንሳዊ ትንተናዎችና መፍትሄዎች ለማግኘትና ትምህርት ቀስሞ ለመውጣት በፍጹም አይቻልም። ብቻ ራሳቸው በሚፈልጉት መንገድ የአፍሪቃን ዕድል ለመወሰንና ሳይንሳዊ የትንተና ዘዴ ነው ብለው ቀድሞ በወሰኑት ፈለግ ብቻ እንዲጓዝ ስለሚፈልጉ እስካሁን ድረስ የአፍሪቃ ችግር የአፍሪቃውያን መሆኑ ቀርቶ „የአውሮፓና የአሜሪካ ምሁራን ችግር“ ሊሆን በቅቷል። ይህ ማለት ግን ለአፍሪቃና ለሌሎች የሶስተኛው ዓለም አገሮች ኢኮኖሚያዊና ህብረተሰብአዊ ችግሮች የተሻለ አመለካከት ያላቸውና መፍትሄ ለማቅረብ የሚችሉ የአውሮፓና የአሜሪካ ምሁራን የሉም ማለት አይደሉም። በፕሮፌሰር ቤን ፊኔና በፕሮፌሰር ኤሪክ ራይነርት ፣ እንዲሁም ሌሎችም ክሪቲካል አመለካከት ባላቸው የአውሮፓና የአሜሪካን ምሁራን የተደረሰበት መደምደሚያ ፣ እስካሁን ድረስ በተለይም የዕድገት ፖሊሲና ቲዎሪ በኤዎ-ሊበራል ኢኮኖሚስቶችና የህብረተሰብ ሳይንስ ምሁራን ነን ባዮች ስለተያዘ ኢንስቲቱሽኖችን ሰብሮ መግባት አልተቻለም። ስለዚህም ፣ የኒዎ-ሊበራል ርዕዮተ-ዓለም በኢንስቲቱሽኖች ላይ የበላይነቱን እስከያዘ ድረስና ከዕርዳታ ሰጪ ደርጅቶች ጋር ያለው መቆላለፍ በዚሁ ከቀጠለ ስለአፍሪቃ ችግርና ፣ በአጠቃላይ ደግሞ ስለ ዕውነተኛ ኢኮኖሚ ዕድገት መወያየት በፍጹም አይቻልም የሚል ነው።

ይህ በራሳቸው በአፍሪቃ ምሁራን አነሳሽነትና አዘጋጅነት የተደረገው ስብሰባ ግን ለውይይት ክፍት መሆኑ ብቻ ሳይሆን የተለያየ አመለካከትና የአስተሳሰብ ጥልቀት ያላቸውን ምሁራንን በመጋበዙ ለውይይቱ ልዩ ገጽታ ሰጥቷል ብል የተሳሳትኩ

አይመስለኝም። በተጨማሪም ፣ ይህ ስብሰባ በየአገሮች ምሁራንም ስለአገሮቻቸው ጠለቅ ያለ ውይይት ማድረግ እንዲችሉ መንገድ ሊከፍት የሚችል ነው ብል ማጋነን አይሆንም። የፖለቲካ ስልጣንን የያዙ የአፍሪቃ መሪዎችን ተግባር ዝቅ አድርጎ ያለየ ፣ ነገር ግን ደግሞ ሳይንሳዊ ውይይትን ከብዙ አቅጣጫ በመመልከት ከታች ወደ ላይ ህብረተሰብአዊ ችግሮችን ለመፍታት እንደሚቻል የጠቆመ ስብሰባ ነው። እንደዚህ ዐይነቱ ስብሰባ ፣ በተለይም ለአንደኛ ላለ የፖለቲካን ጉዳይ ብቻ ከፍ አድርጎ በማየት ለሌሎች ሳይንሳዊ ጉዳዮች እምብዛም ቦታ ለማይሰጠው ምሁር ጥሩ ትምህርት መስጠት እንደሚችል ይህ ፀሀፊ ለመገንዘብ ችሏል። የሚያሳዝነው ግን ፣ በዚህ ስበሰባ ላይ ሌሎች ኢትዮጵያውያን ሊገኙ አልቻሉም። በተጨማሪም ፣ የአፍሪቃ ኤምባሲ ሰራተኞች ተገኝተው ከእንደዚህ ዐይነቱ ስብሰባ ብዙ ነገር መማር ሲችሉ ፣በመክፈቻው ዕለት ለጥቂት ሰዓታት ተገኝተው የመክፈቻውን ንግግር አዳምጠው የወጡት የአንጎላ ፣ የሞዛምቢክና የናይጀሪያ አምባሳደሮች ብቻ ናቸው።ይህም የሚያረጋግጠው የአፍሪቃ አምባሳደሮች ለአህጉራቸውና ለየአገሮቻቸው ስለዕድገትና ህብረተሰብአዊ ለውጥ ያላቸው አመለካከት አልቦ መሆኑን ነው ።

## የችግሮቹ አቀራረብ ዘዴ!

እንደሚታወቀው ስብሰባው ሲዘጋጅ አዘጋጆቹ ስብሰባው ጥልቀትና ሰፋ እንዲል በማድረጋቸው ጥናት አቅራቢዎችም እንደዚሁ የአፍሪቃን ችግር በአፍሪቃ ምሁራን መነጽር መመልከትና መፍትሄ ለመስጠት መሞከር ያስፈልጋል ከሚለው የአሰራር ዘዴ በመነሳት ነው ተዘጋጅተው የመጡት። አቀራረቡም በአንድ በኩል ፣ በመጠኑም ቢሆን በቅኝ ግዛት ዘመን የነበረውን የአፍሪቃ ሁኔታ የዳሰሰ ሲሆን ፣ በተለይም አትኩሮ የተሰጠው ቅኝ ግዛት ጥሎት በሄደው ቅሪትና ከዚያ በኋላ የተፈጠሩትን የኢንስቲቱሽኖችን ሚናና የማህበረሰብአዊና የኢኮኖሚ አወቃቀር ጠለቅ ብሎ በመመልከት ነው። በመሆኑም  አፍሪቃ ከሌሎች አገሮች ፣ በተለይም ጃፓን ፣ ደቡብ ኮሪያ ፣ታይዋንና ማሌዢያ እንዲሁም ቻይና ጋር ስትወዳደር ቢያንስ የእነሱን ፈለግ ለመያዝ ያልቻለችበት ምክንያት ምንድ ነው? የሚል የአቀራረብ ዘዴ ነው በመያዝ ውይይቱን ለማካሄድ የተሞከረው። ስለዚህም ፣ ስለአፍሪቃ ኋላ-ቀርነት ሲወራ አንድ ነጠላ ነገርን ብቻ እንደምክንያት ጨብጦ መወያየት እንደማይቻልና ፣ በተለይም ደግሞ የአፍሪቃን የታሪክና የህብረተሰብ ሂደትና አወቃቀር ጠለቅ ብሎ መመልከትና በትንተና ውስጥ ማካተት ችግሩን የበለጠ ለመረዳትና ተግባራዊ ሊሆን የሚችል መፍትሄ መስጠት የሚያስችል ሁኔታ መፍጠር ይቻላል ተብሎ ነው ግምት ውስጥ የተገባው። በመሆኑም ፣ አፍሪቃ ከሌሎች የአሺያ አገሮች ጋር ስትነፃፀር የሚለያት አንደኛ ፣ ከአስራ አምስተኛው ክፍለ-ዘመን ጀምሮ ሰውን መሚጠጥ ተግባራዊ የሆነበት የባርያ ንግድ ያስከተለው ህብረተሰብአዊ መመሰቃቀልና ተከታታይነት ያለው ስራ እንዳይሰራ የተተከለባት ችካል ፣ ሁለተኛ ፣ በ19ኛው ክፍለ-ዘመን አፍሪቃን ለመቀራኘት የተደረገው የቅኝ አገዛዝ ፖሊሲና ፣ ከውስጥ ገበሬውን ማፈናቀልና የስራ-ክፍፍል እንዳይዳብር ማድረግ ፣ ሶስተኛ ፣ ከቅኝ ግዛት መለቀቅ በኋላ ሁኔታው በረቀቀ መልክ መካሄድና ብዙ የአፍሪቃ አገሮችም ራሳቸውን እንዳይችሉ ይደረግባቸው የነበረው ግፊትና አሻጥር ፣ አራተኛ ፣ በአፍሪቃ ውስጥ ስልጣንን የያዘው ኤሊትና ከሱ ጋር በሺህ ድሮች የተሳሰረው ምሁር ዕድገትን የማይፈልግ ወይም ደግሞ የሚቀናቀን መሆኑና ፣ ለውጭ ኃይሎች አጎብዳጅ መሆኑ ፤ አምስተኛ ፣ በተለይም በአሁኑ ወቅት ስልጣንን የያዘውና በፓርቲ ስም እዚህና እዚያ የሚረገጡት በምሁርነት በፍጹም ሊታሙ እንደማይችሉና ፣ ከጥራት ይልቅ ብዛት አይሎ በመውጣቱ ብዙ ፓርቲዎችንና በስልጣን ላይ ያለውንም ጨምሮ ጠለቅ ያለ ምሁራዊ አስተሳሰብ ያለውን ግለሰብ ሁሉ ማግለል እንደሙያ ተደርጎ በመወሰዱ ዕድገትንና መሰረታዊ የህብረተሰብ ለውጥን በፍጹም ማምጣት አልታቸለም ፤ አይቻልምም የሚል ነው። ስድስተኛ ፣ ከዚህ ጋር ተያይዞ የውጭ የስለላ ኃይሎች እንደዚህ በጥልቀት ማሰብ የማይችለውን በማሳደድና በጥቅም በመግዛት በህዝቡ ላይ እንዲነሳ ያደርጋሉ። በዚህም ምክንያት በስለላ ድርጅትና በወታደር የተከበበ ኃይል በመፍጠር የፀረ-ዕድገቱ ዘመን እንዲራዘም ያደርጋሉ። ሰባተኛ ፣ በስልጣን ላይ ያሉት አገዛዞች ለምን ስልጣንን እንደጨበጡ ሊገነዘቡ የማይችሉና ፣ ችግሮች አፍጠው አግጠው እየታዩ ራሳቸውን ለመጠየቅ ዝግጁ ያልሆኑ ፣ በመሆኑም ሞራላዊና ህሊናዊ ኃላፊነት የማይሰማቸው ፍጡሮች በየቦታው ተቀምጠዋል የሚል ትንተና ነው የተሰነዘረው። አብዛኛዎቹም ህሊናቸው ተሟጦ ያለቀ የሚመስሉና ፣ አንዱ ምሁር እንዳቀረበው መንፈሳዊ ጥንካሬ የሌላቸውና አገርን ለመሸጥ የተዘጋጁ የሆኑ እንደሆን ነው ግንዛቤ ውስጥ የተገባው።  በዚህም ምክንያት ፣ ሁኔታው ለለውጥ አስቸጋሪ እንደሆነና ፣ በአንዳንድ ቦታዎችም የየአገሩ መሪዎች የህብረተሰቡን ችግር መፍታት ወደ ማይችሉበት ደረጃ ስለደረሰና ሁኔታውንም

ስለሚያመሰቃቅሉ ፣ ለጦር ትግል የሚጋብዝ ሁኔታ መፈጠሩ ምሁራዊ እንቅስቃሴ አካሂዳለው ለሚለው አስቸጋሪ ሁኔታ እንደተፈጠረበት ተጠቁሟል። በዚህ ላይ የውጭ ኃይሎች የየአገዛዞችን የውስጥ ድክመት በመገንዘብ ፣ በአንድ በኩል በመንግስት መኪና ውስጥ ሰርገው ሊገቡ የሚችሉበት ሁኔታ እንደተመቻቸና ፣ በዚያውም አፍሪቃን የጦር አውድማ ለማድረግ ሲውጠነጠን ፣ በሌላ ወገን ደግሞ የጥሬ ሀብቷን ለመቃረም ትልቅ ፍልሚያ ውስጥ የተገባበት ሁኔታ ነው የሚታየው። ይህንን በሰፊውና ጠለቅ ባለ ሁኔታ ያጠናው ምሁር ከምንግዜውም የበለጠ የጠራ ምሁራዊና ሳይንሳዊ ትግል ማድረግ እንደሚያስፈልግ አስገንዝቧል።

## ውይይት የተደረገባቸው ነጥቦች !

ከላይ እንደቀረበው ችግሮቹ ሰፊና ጥልቀት ያላቸው ሲሆኑ ፣ የመጀመሪያው ተጋባዥ እንግሊዛዊ ፕሮፌሰርና የቋንቋ ምሁር ፣በራስ ቋንቋ አለመማርና ለመናገር ፈቃደኛ አለመሆን ፣ እንዲሁም ደግሞ ቋንቋ በአንድ አገር ዕድገት ላይ ስለሚኖረው ሚና ለመገንዘብ ያለመቻል ብዙ የአፍሪቃ አገሮችን ለማቆርቆዝ ተችሏል ብለዋል። አብዛኛዎቹ የአፍሪቃ አገሮች የራሳቸው ቋንቋ እያላቸው ለስራና ለንግግር የሚጠቀሙበት ቋንቋዎች ፈረንሳይና እንግሊዘኛ በመሆኑ በተማረውና በአልተማረው ህዝብ ዘንድ ትልቅ አለመግባባት እንዳለና ፣ስልጣን የጨበጡትም ሆነ ሌላው ምሁር ከህዝቦቻቸው ተነጥለው በልዩ ዓለም ውስጥ እንደሚኖሩ ጠቁመዋል። በፕሮፌሰሩም ግሩም አቀራረብ ፣ ቋንቋ በአጠቃላይ ሲታይ ጭንቅላትን የማዳበርና ጠለቅ ያለ አስተሳሰብን ለመያዝ የሚያስችል ኃይል አለው። ማንኛውም ልጅም ሆነ ያደገ ሰው ባደገበት ቋንቋ ቢነጋገርና ቢሰራ የህብረተሰቡን ችግር የመረዳት ኃይሉ ከፍ ያለና ለውጥንም ለማምጣት የተዘጋጀ ይሆናል ብለዋል። በዚህም ምክንያት *በቋንቋ ፣ በጭንቅላት መዳበርና በፍልስፍና መሀከል ግኑኝነት* መኖሩን ሲጠቁሙ ፣ አፍሪቃ ካለችበት ሁኔታ ለመላቀቅ የምትችለው የኢምፔሪያሊስቶችን የመነጋገሪያ ቋንቋ ትታ ራሷን ማግኘት የቻለች እንደሆን ብቻ ነው ብለዋል። ይህ ማለት ግን ማንኛውንም የውጭ አገር ቋንቋ እንደ ቋንቋ መማር አያስፈልግም ማለት እንዳይደለ ፕሮፌሰሩ አስምረውበታል። ስለዚህም ፣ አፍሪቃ የራሷ ሬናስናስ ያስፈልጋታል ፤ ለዚህም ዋናውና የመጀመሪያው ቁልፍ ቋንቋ ሲሆን ፣ በፕሮፌሰሩ አነጋገር ፣ እንደኛ ያለ አደገኛ ምሁር ራሱን ለመለወጥ ዝግጁ መሆን እንዳለበት አሳስበዋል። ምሁሩ ቋንቋ ለዕድገትና ለአጠቃላይ ህብረተሰብአዊ ለውጥ ያለውን ትርጉም በመረዳት ኃላፊነቱን ለመወጣት መቻል እንዳለበት አስገንዝበዋል።

በሀለተኛው ሴሽን ላይ የቀረበው ፣ ብዙ የአፍሪቃ አገሮች ከቅኝ አገዛዝ ስር ከተላቀቁ ጀምሮ የተከተሉት የኢኮኖሚ ፖሊሲን የሚመለከት ሲሆን ፣ በአንድ ከናይጀርያ ተጋብዘው በመጡ የዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰር የቀረበ ግሩም ሀተታ ነው። በፕሮፌሰሩ ገለጻ ፣ አብዛኛዎቹ የአፍሪቃ አገሮች ነጻ ከወጡ ጀምሮ የራሳቸውን የኢኮኖሚ ፖሊሲ ለመንደፍ ያልቻሉና የየህብረተሰቦቻቸውን ዕድገት ለመወሰን ያልቻሉ ናቸው ብለዋል። በፕሮፌሰሩ አገላለጽ ፣ አብዛኛዎቹ የአፍሪቃ አገዛዝ የራሳቸው ፍልስፍናና አመለካከት ስለሌላቸው እንደ ከብት በመነዳት የውጭ አማካሪዎች የሚሰጧቸውን ፖሊሲ በመቀበልና ተግባራዊ በማድረግ ሊወጡ የማይችሉት ዕዳና ችግር ውስጥ ሊገቡ በቅተዋል ብለዋል። ስለሆነም ፣ በየአስር ዓመቱ ስሙን እየለዋወጠ የሚመጣ የኢኮኖሚ ፖሊሲ የአህጉሪቱን የጥሬና የገንዘብ ሀብት እንዲሟጠጥ ያደረጋና የሚያደርግ ነው። በተጨማሪም ፣ ፖሊሲዎቹ በሙሉ የውስጥ ገበያን ለማዳበርና የስራ-ክፍፍል እንዳይስፋፋ የሚያደርጉ በመሆናቸው ፣ ሀብት ሊባክን በቅቷል ብለዋል። እንደናይጄሪያ ያሉት የተትረፈረፈ የዘይት ሀብት ያላቸው አገሮች ሌላው ቢቀር እንኳ በምግብ ራሳቸውን እንዳይችሉና በዕዳ እንዲተበተቡ ተደርገዋል ይላሉ ፕሮፌሰሩ። ናይጄሪያ ወደ ውጭ ጥሬ ዘይት እየላከች በአንፃሩ ደግሞ 90 በመቶ የሚሆነውን የነዳጅ ፍላጎቷን ከውጭ በውድ ታስመጣለች ብለዋል። በፕሮፌሰሩም ሆነ በሌሎች አገላለጽ ፣ የዘይት ሀብት ከመገኘቱ በፊት ናይጄሪያ በምግብ ራሷን የቻለች ብቻ ሳትሆን ወደ ውጭም የምትልክ እንደነበረች አስረድተዋል። አሁን ግን ምግብ ማስመጣት ብቻ ሳይሆን ፣ መንግስት የእርሻው መስክ እንዲበለጽግ ምንም ርዳታ እንደማያደርግና ሁኔታው በዚህ ከቀጠለ ትልቅ ህብረተሰብአዊ ቀውስ ሊመጣ እንደሚችል አስረድተዋል። ምክንያቱም ፣ በገጠሩ ውስጥ ምንም ዐይነት መዋዕለ-ነዋይ ስለማይካሄድና የስራ መስኩም እየጠበበ ስለሚመጣ ብዙ ሰው ገጠሩን እየለቀቀ ወደ ከተማ እንዲሰደድ ይገደዳል። ይህ ሁኔታ ደግሞ የግዴታ በከተማዎችም መጨናነቅን ከማምጣቱም ባሻገር መንግስት በቀላሉ ሊቋቋመው የማይችለው የወንጀል ተግባር ይስፋፋል ብለዋል። በአንዱ ተሳታፊ አገላለጽም ፣ በተለይም በኤሊቱ ዘንድ የእርሻ ባህል ምን እንደሆነ ግንዛቤ ውስጥ ባለመገባቱና ከውጭ የሚመጣ ምግብ ከፍተኛ ቦታ ስለሚሰጠው እርሻን የመናቅ አዝማሚያ ይታያል ብለዋል። አያይዘውም ከውጭ የሚመጡ ምግቦች ብዙ ጠንቆችንም ይዘው እንደሚመጡና ይህ በራሱ

ደግሞ ተጨማሪ ወጪ እንደሚያስወጣ በመጠቆም ከዚህ አዙሪት ውስጥ ለመውጣት ትልቅ ትግል እንደሚያስፈልግ አሳስበዋል። ምክንያቱም አዲስ በተከሰተው የአመጋገብ ዘዴ የስልጣኔ በሽታዎች የሚባሉት ስለተስፋፉና ስለሚስፋፉ ለህክምና የሚወጣውን ወጪ ከፍ ያደርገዋል። ተናጋሪው በመቀጠልም ፣ ግብርና በተለይም በወጣቱ ስለሚናቅና በመንግስትም ምንም የማበረታታት እርምጃ ስለማይወሰድ ወደ ፊት ከፍተኛ ችግር እንደሚፈጠር ጠቁመዋል።

ከዚህ ቀጥሎ ሙስና በስልጣን ላይ ያለውን ኃይል ተብትቦ እንደያዘውና በብዙ ቢሊዮን የሚቆጠር ከዘይት ሽያጭ የሚገኝ ገንዘብ የት እንደሚገባ አይታወቅም። ሙስና ስር ከመስደዱም ባሻገር ፣ በሙስና የናጠጠው ሀብታም ነኝ ባይ በሌላ ዓለም ውስጥ እንደሚኖር ዐይነት ሁኔታ ነው የሚታየው። በተለይም ራሱ የመንግስት ባለስልጣኖችና ከፍተኛ የፓርቲ ሹማምንት በሙሰና የዘፈቁ ስለሆነና ርስ በራሳቸው የተሳሰሩ ስለሆነ ለመዋጋት በጣም ያሰቸግራል ብለዋል። ይህ ዐይነቱ የሙስናና አዲስ ዐይነት የአኗኗር ሁኔታ ደግሞ የፀፅጥታን ችግር አስከትሏል። ሀብታሙ ራሱን ለመጠበቅ ሲል ቤቱንና ግቢውን ልዩ የጥበቃ ስልት እንዲበጅለት እንዲያደርግ ተገዷል።

በሁለተኛው ቀን ባህልን የሚመለከት ጥናት የቀረበ ሲሆን ፣ አንድ አሜሪካን አገር የሚማር ናይጄሪያዊ ፣ ለመሆኑ ከቅኝ ግዛት በፊት ናይጄሪያ ባህል አላት ወይ? ባህልስ ስባል ምን ማለት ነው? ብሎ ሰፊ ገለጻ ለመስጠት ሞክሯል። በምሁሩ አገላለጽ ፣ የዛሬውን የናይጄሪያ ባህል የፖስት ኮሎኒያል ባህል ነው ብሎ መግለጽ እንሚቻል ሲያስረዳ ፣ ናይጄሪያ የብዙ ብሄረሰቦች አገር እንደመሆኗ መጠን ፣ ይህ ነው የናይጄሪያ ባህል ብሎ መናገር እንደማይቻል አስረድቷል። በተጨማሪም ፣ ባህል ቋሚ ነገር አይደለም ፤ ከሰዎች የአኗኗር ስልት ፣ የአሰራርና ከዕድገት ሁኔታ መሻሻል ጋር ሊለወጥ እንደሚችልና ፣ ዛሬ ባህል ብለን የምንጠራው ከሁለት መቶና ከሶስት መቶ ዓመት በፊት ከነበረው እንደሚለይ ለማስረዳት ሞክሯል። አብዛኛዎቹ ተጋባዦች ከተለያዩ ጎሳዎች በመምጣታቸው ይህ ጉዳይ በጣም አጨቃጭቋቸዋል። እንደሚታወቀው እንደባህል የሰውን ጭንቅላት የሚከነክን ጉዳይ የለም። ለማንኛውም አንዱ ምሁር ለማስረዳት እንደሞከረው ፣ ባህል በህንፃ ስራ ፣ በሙዚቃ ፣ ተፈጥሮን በመቃኘትና በስእል ፣ በአለባበስ ፣ በአነጋገርና በአካሄድ ፣ በምግብና በስራ... ወዘተ. ሊገለጽ የሚችል ሰፊ ትንተና ሊሰጠው የሚያስፈልገው ሲሆን ፣ የአንድ አገር ባህል ይህ ነው ብሎ በአንድ ቃል ለመግለጽ እንደሚያሰቸግር አስረድቷል። በአንድ አገር ውስጥም ከሀብት ሽግሽግ ጋር የተያያዙ ልዩ ልዩ ባህሎች ሊኖሩ እንደሚችሉና ፣ የአንድ አገር ባህል በአንድ ነገር ሊገለጽልና የአንድ አገር ህዝብ ባህልም ይህንን ይመስላል ብሎ መናገር እንደማይቻል ታምኖበታል። ባህልም ተወራራሽ እንደመሆኑ መጠን ፣ በታሪክ ውስጥ በተለያዩ መንገዶች ባህሎች በመጋጨት ለዕድገትም አስተዋጽዎ እንዳበረከቱ ለመጠቆም ተችሏል።

የሚቀጥለው ተናጋሪም ፣ የአንድ ዩኒቨርሲቲ ምሁር ሲሆኑ ፣ ስነ-ጽሁፍ አንድን አገዛዝና ህብረተሰብ ለመለወጥ ስለሚኖረው ሚና በጥሩ ሁኔታ አስረድተዋል። በሊትሬቸር የአንድን ህብረተሰብ አኗኗር መግለጽ ይቻላል። በሊትሬችር አንድን አገዛዝ በጉራማይሌ መልክ መተቸት ይቻላል። ስለሆነም ፣ አገዛዙን መግራት ይቻላል። በሊትሬችር ተፈጥሮን መቃኘት ይቻላል። ባጭሩ ፣ ስነ-ጽሁፍ ልዩ የጭንቅላት ስራ እንደመሆኑ መጠን ፣ ከታወቀበት አንድን አገዛዝም ሆነ ህብረተሰብ በዚህ አማካይነት ቀስ በቀስ መለወጥ ይቻላል ብለዋል ምሁሩ። አንዱ ተሳታፊ ለማብራራት እንደሞከረው ፣ ከስነ-ጽሁፍ በተጨማሪ ፣ ድራማና ስዕል የሰውን ስሜት የመንካትና የመማረክ ኃይላቸው ከፍተኛ ስለሆነ በዚህ ቢታሰብበት በአጭር ጊዜ ውስጥ የመረቃ ውጤት ለማግኘት እንደሚቻል አስረድቷል። በአውሮፓ ታሪክ ውስጥ ከግሪክ ስልጣኔ እስከ ጀርመኑ ክላሲኮች ድረስ ከተጻፈ ይልቅ ንግግርና ትዕይንት ሰዎችን የመሳብና የማስተማር ኃይላቸው ከፍተኛ እንደሆነና ፣ በተለይም የማንበብ ባህል በሌለባቸው አገሮች ለዚህም ክብደት መስጠት እንደሚያስፈልግ ጠቁሟል።

ወደ መፍትሄውም ስንመጣ ፣ ከአካባቢ መቆሸሸ አንስቶ ፣ እስከ እርሻና የምግብ ቀውስ እንዲሁም ደግሞ አጠቃላዩን ችግር ስለመፍታት ስትራቴጂ ፣ በአቅራቢዎቹ በግሩም መልክ ተገልጿል። በተለይም ፣ አንድ ማስትሬቷን የምትሰራ የማቲማቲክ ተማሪ ፣ከኢንዱስትሪ የሚወጣን ቆሻሻ በማቲማቲካል ሞዴል እንዴት መፍታት እንደሚቻል ግሩም በሆነ መልክ አስረድታለች። በሌላ ወገን ደግሞ ፣ ከዚህ ጸሀፊ ለአቅራቢዋ የቀረበው ጥያቄ ፣ ቆሻሻ ከመከሰቱ በፊት ይህንን ሊያስታግስ ወይም ሊያሰወግድ የሚችል የማቲማቲክስ ሞዴል መስራት ይቻላል ወይ? ብሎ ላቀረበላት ጥያቄ ፣ጥያቄው በጣም ጥሩ እንደሆነና እንደምታስብበትም ቃል ኪዳን ገብታለች። ከዚህ ጋር ተያይዞ የቀረበው ጥናት

የአፍሪቃን ችግር ከብዙ አቅጣቻ (Multivariant Analysis) ማየትና መፍትሄውም የተደጋገፈ እንደሆነ አንድ የናይጄሪያ ምሁር እጅግ ግሩም በሆነ መልክ በፓወር ፖይንት አቅርቧል። በምሁሩ አገላለጽ ፣ በቅጡ ባለማሰብ ብዙ ስህተቶች መሰራታቸውን ጠቁሞ ፣ በአፍሪቃ ውስጥ ያለው ችግር የነገሮችን ተወራራሽነት ፣ተጽዕኖና ውስብሰብነት በሚገባ ለማጥናት አለመዘጋጀትና አለመፈለግ በየጊዜው አዳዲስ ስህተቶች እንዲፈጸሙ በር ይከፍታል። ስለዚህም ፣ በአንድ በኩል የነገሮችን አመጣጥ በሚገባ ማጥናት ሲያስፈልግ ፣ እንደዚሁም መፊትሄ መፈለግ የሚቻለው በአንድ ነገር ላይ ብቻ በማትኮር ሳይሆን በአጠቃላይና በተከታታይ እርምጃ የተወሰደ እንደሆን ነው ብሏል። በሌላ በኩል ደግሞ ችግሮች እስኪደራረቡ ድረስ አለመጠበቅ በተቻለ መጠን ቶሎ ብሎ መፍትሄ ለመሻት መጣር አጠቃላይ ህብረተሰብአዊ ቀውስ እንዳይፈጠር ይረዳል። ከዚህ በተረፈ ፣ በሁሉም ተካፋይ የተደረሰበት መደምደሚያ ፣የአፍሪቃን ችግር መፍታት የሚቻለው ከሌሎች ነገሮች ባሻገርም በሳይንስና በቴክኖሎጂ አማካይነት ነው።አፍሪቃ የግዴታ የኢንዱስትሪ አብዮት ማካሄድ አለባት ፤ በጥሬ-ሀብት አምራችነት ብቻ ወደፊት አጥጋቢ ዕድገትን ልታመጣና የህዝቦቿን ፍላጎት ማሟላት አትችልም የሚል ድምደማ ላይ ነው የተደረሰው። በተጨማሪም የአፍሪቃ ህዝብ ፣ በተለይም ደግሞ ኤሊቱ ድርቅ ካለ አስተሳሰቡ መላቀቅና አእምሮውን በአዲስ አስተሳሰብ ማነፅ መቻል አለበት። በሁሉም ተካፋይ የተደረሰበት ስምምነት የአስተሳሰብ ለውጥ ወይም የባህል ለውጥ እስካልተደረገ ድረስ ህብረተሰብአዊ ለውጥ ለማምጣት እንደማይቻል ነው። በሌላ አነጋገር ፣ በአፍሪቃ ውስጥ ያለው ችግር የራስን ሚና መረዳት አለመቻል ፤ የማሰብ ኃይልን ተጠቅሞ በግልጽ የሚታዩ ችግሮችን ለማስወገድ አለመጣርና ፣ በራስ ክልል ብቻ እየተሽከረከሩ መኖር ችግሮች እንዲቆለሉና እንዲደራረቡ እንዲሁም መፍትሄ እንዳይገኝላቸው ለማድረግ ተችሏል። ይህ ችግር የናይጄሪያ ብቻ አይደለም ፤ የጠቅላላው የጥቁር አፍሪቃ ችግር ነው።

በአጠቃላይ ሲታይ ጉባዔው ለብዙዎቻችን ትምህርት የሰጠ ሲሆን ፣ የአንድ ህብረተሰብ ችግርና መፍትሄ በቀላሉ መታየት እንደማይችልና ሰፋና ጠለቅ ያለ ዕውቀትን የሚጠይቅ መሆኑን ነው። በተጨማሪም እያንዳንዱ በየሙያው ጠለቅ ብሎ ማሰብ መቻል እንዳለበትና መፍትሄ ለመፈለግ አስፈላጊውን ጥናት ማድረግ እንደሚያስፈልግ ትምህርት ጥሎ ያለፈ ጉባዔ ነው።

## እኛስ ከዚህ ምን እንማራለን ?

እስካሁን ድረስ እንደተከታተልኩት ፣ በእኛ በኢትዮጵያኖች ዘንድ ፖለቲካ ትልቅ ክብደት ይሰጠዋል። ሁሉም ወደ ፖለቲካ ስለሚያዘነብል መሰረታዊ የህብረተሰብ ጥያቄዎች ክብደት አይሰጣቸውም። አብዛኞቻችን ከፖለቲካ በስተቀር ሌሎች ነገሮችን መስማት የምንፈልግ አይመስለኝም። ፖለቲካ አስፈላጊ የሆነውን ያህል ፣አንድ ግለሰብም ሆነ ህብረተሰብ ለፖለቲካ ብሎ አይኖርም። ፖለቲካ ግቡን ሊመታ የሚችለው መሰረታዊ የህዝብ ጥያቄዎች ሲመለሱና አገርን የመገንባት ጉዳይ መስመር ሲይዝ ነው። ወደ አንድ አቃጣጫ የሚደረግ ትግል አንድን ህብረተሰብ ወደ ኋላ እንዲቀር ያደርገዋል። በሆነ ባልሆነው ጉዳይ ላይ ሁሉ ንትርክ ውስጥ እንዲገባ ይገፋፋዋል። ፖለቲካም ራሱ ሳይንስ እንደመሆኑ መጠን ከሳይንስ አንፃር ካልታየና ካልቀረበ በስተቀር መፎከሪያ ሆኖ ይቀራል። ከንጹህ የፖለቲካ ትግል ተላቀን በተማርነው ሞያ እየገፋን ይህንን በጥናት መልክ ብናቀርብ የህብረተሰብአችንን ችግር የመፍታት ኃይላችን ከፍ ማለቱ ብቻ ሳይሆን ጠለቅ ብለንም እንድናስብ ይረዳናል። የዛሬው አንገብጋቢ ጥያቄም መፍትሄ መፈለግ እንጂ በሆነው ባልሆነው ንትርክ ውስጥ በመግባት ለስልጣኔ እንቅፋት መፍጠር አይደለም። ከዚህ ጉባዔ የተማርኩት ይህንን ቁም ነገር ያዘለበት ትልቅ ትምህርት ነው። መልካም ንባብ!

ፈቃዱ በቀለ
fekadubekele@gmx.de